## አንገት - አልቦ ራስ

ከገንባው

እቆጥረው ያቃተኝ፣ ሌቱን በጄ ሳለ፣
ዓይኔን ተጠራጠርኩ፣ ቀን እየጎደለ።
--
ሰው እንዲህ ሲጎድል፣ በአንደዜ ቀን፣
ለዳበሳ ባጣው፣ ራስ ራሱን፣
ወገቤን አጉብጬ፣ ከመሬት ደርሼ፣
ውር ድንብሬን፣ ባስስ ተጎ’ብሼ፣
አገኘሁት ሁሉን፣ ተቀንጥሶ አንሶ፣
አንገት - አልቦ ራሱ፣ ሆዱን ተንተርሶ።
*********************************************

## ገደል ግቢ ምርጫ

ሳላይ የሸሸሁሽ፣ ባጣብሽ ታዛቢ፣
ዛሬ ተኳኩለሽ፣ ደምቀሽ በአጃቢ፣
ቢያንቆላብሱሽም፣ አውሮፓ አሜሪካ፣
አላማረብሽም፣ ምርጫ በአፍሪካ።

ከንግዲህ አልመርጥም፣ ለፌዝ ለለበጣ፣
ካርተርን ተክቶ፣ ክርስቶስ ካልመጣ።
ድሮም ትቼው ነበር፣ የምርጫን ነገር፣
ምረጥ መባል ሲያዝ፣ አንበሳና ነብር። (የደርጉን ምርጫ ያስታውሷል)
ዘንድሮ ስቼ እንጂ፣ “ንብ” መስሎ ቢመጣ፣
ቆሻሻው ማር መስሎኝ፣ በጉዴ እስኪወጣ።
አሁንም ሞኙ ሰው፣ ሳጠራው ቤቴን፣
ዝምቡን እሽ ብዬ፣ ስደግስ ሞቴን፣
ዝምብም ብቻ አልነበር፣ የሱ ድብቅ ስራ፣
እባብ ጭምር ሁኖ፣ ይናደፍ ጀመራ።
ነብርና አንበሳን፣ ትናንት ፈርቼ፣
የጠላሁትን ‘እርም’፣ ማር መስሎኝ በልቼ፣
መለስ ሲባል ለካ፣ ንባም ዝምባም ፊቱ፣
ጉዱ ከሁዋላ ነው፣ የእባብነቱ።

ይብስ የሚቆጨው፣
የተወጋሁትን፣ ‘ኔው እንዳላክመው፣
በዓለም አደባባይ፣ ማንከስ መጎተቴ፣
ታስገዳይ - ገዳዬ፣ ሽንጎ መገኘቴ።
የተሰማሁ መስሎኝ፣ ተጣራሁ አምርሬ፣
ዴሞክራሲና ሞት፣ ካዳይ ከናጅሬ፣
ምንም አላገኘሁ፣ ቀረሁኝ አፍሬ።
ለተንግዲህ ምርጫ፣ በማርያም እግር ጎሜዝ፣
ከተማሰለቻት፣ ለድሆች በማገዝ፣
ከአጅሪት በቀር፣ በትልቅ ስም መጥቶ፣
ህሊናውን ሽጦ፣ ወድቆ ያማ - ሞቶ።
ምን ሊፈይድ ብዬስ፣ ያውሮፓ ታዛቢ፣
ተመራጭ የሌለሽ፣ ምርጫ ገደል ግቢ።